# <u>ትንሽ ወግ ስለ ደምሴ ዳምጤ</u>

የደምሴን መታመም ከሰማሁ ወዲህ ያደረበት የስኳር ሕመም (ዳያቤቲክስ) የዓይኑን ብርሐን ከማሣጣት በዘለለ ይህን ያህል ለሕይወቱ ያሰጋል ብዬ አልገመትሁም፡፡ ለመጀመሪያ ሕክምና ወደ ባንኮክ ተጎዞ ሲመለስ የአንደኛው ዓይኑ ብርሐን ማጣት አስከፊ ዜና ቢኖርም የቀኝ ዓይኑ ብርሐን ወደ 20 ከሙቶ የተመለሰ መሆኑንና ሊሻሻል እንደሚችል በመስማቴ ተመስገን በያለሁ፡፡

መቼም ስለደምሴ ዳምጤ የስፖርት ዘገባ በተለይ በስሜት ተውጦ የሚናገራቸው ነገሮች ብዙዎቻችን የምናስታውሣቸው ናቸው፡፡

## ሞስኮ ኦሎምፒክና ደምሴ

የስፓርት ዜናውን ሱቅ ስንላክ ከሚጠበቅብን ጊዜ በልጅነት ልብና እግር በሩጫ ሰርቀን ዘውዴ ጠጅ ቤት ከጠጅ ቀጂው ብርሃኑ ኩርኩርም ጋር ድብብቆሽ እየተጫወትን እነ ምሩፅ ይፍጠርን ያየንበት ወቅት ነበር፡፡ ከዚያም ዳምሴ ዳምጤ ስሜት እየተናነቀው "ጀግናው ምሩፅ ይፍጠር" በመጀመሪያ በ10 ሺህ ሜትር ከዚያም 5000 በድጋሚ በማሸነፍ ሁለት የወርቅ ሜዳሊያዎችን እንዳገኘና ይፍጠር ዘ ሽፍተር የሚል ቅጥያ ስም መጎናፀፉን ሲዘግብ የሩጫው ሜዳ አገላለፁ በጣም አስደማሚ ነበር፡፡

"ዜና ኦሎምፒክ ከሞስኮ፤ ሪፖርተራችን ደምሴ ዳምጤ እንደተከታተለው" ይላል የግርማ ነጋሽ ድምጽ፤

የሞስኮ ኦሎምፒክ ድል በሙዚቃም የታጀበ ነበር፡፡

"የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ እንኳን ደስ ያለህ
ጀግናው ምሩፅ ይፍጠር አሸነፈልህ"

ይህ ሕብረ ዝማሬ በወቅቱ በምድር ጦር ኦርኬሰትራ የተዘመረ ይመስለኛል፡፡ መዝሙሩ መሐል ላይ ምሩፅ ምሩፅ ምሩፅ የሚል መስመር አለው፡፡ ታዲያ የዚህ ድል ቀጣይነት ያሣሰበው ደምሴ ልክ ድሉ በተገኘ በዓመቱ "የዛሬ ዓመት በዚቹ ዕለት፤ በዚቹ ሰዓት" የሚል ዘገባ የምሩፅ ይፈጠር ስም የሚጠራበትን የዝማሬውን መስመር በመውሰድ በትዝታ ይዞ የሚሔድ እና በቀጣይነትም የሚያነሣሣ ኘሮግራም ሠርቶ ነበር፡፡

በሌሎቹ ሁለት ኦሎምፒኮች ዘጋባው አብዛኛው ሰው የሚየስታውሰውና በመሆኑ ላለማሰልቸት አልፌዋለሁ፡፡

## ደምሴና ብሔራዊ የእግር ኳስ ቡድን

ከ31 ዓመታታ በፊት ብዬ ልጽፍ ጀመርኩና የሰሞኑ ተደጋጋሚ ቃል እንዳይመስልብኝ ብዬ ሰጋሁ፡፡ በዚያ የብሔራዊ ቡድናችን የመጨረሻ የተሣትፎ ማጣሪያ ደምሴ ከብሔራዊ ቡድናችን ግጥሚያ በተጨማሪ ኮናክሪ ላይ አይቶት ስለተደመመበት ነገር በሪፖርቱ ላይ አካትቶ ነበር፡፡ ኮናክሪ ስታድየም ብሐሪዊ ቡድናችን ልምምድ ሲያደርግ ለማየት ተገኝቷል፡፡ እና አዛ ሲደርሱ በሰታድየሙ ሌላኛው በር ታዳጊዎች ኳስ ይዘው ወደ ሜዳ ሲገቡ ያያል፡፡ "በቅርብ የነበረውን የአገሩ ተወላጅ /ምናልባት የኢትዮጵያን ቡድን እንዲረዳ የመደበ ሰው ይመስለኛል/ እነዚህ ልጆች ምንድናቸው ብዬ ጠየቅሁት" ይላል ደምሴ፡፡ ተጠያቂውም ልጆቹ እግር ኳስ ሊለማመዱ የመጡ መሆኑን ይነግረዋል፡፡ በሁኔታው የገረመው ደምሴ "ታዲያ ስታደየም ገብተው ሲጫወቱ አትከለክሏቸውም ወይ" ብሎ ጥያቄውን ያስከትላል፡፡ ያገኘው ምላሽ ግን እነርሱን ከልክለን አሁን ያለውን ብሔራዊ ቡድን ነገ ማን ይተካዋል የሚል ምላሽ ሲሰጠው በነገሩ እጅግ የተገረመው ደምሴ "እነዚህ ልጆች እኛ አገር ቢሆኑ ኖሮ ይሔሌ ፖሊስ እያራወጠ ድራሻቸውን ያጠፋው ነበር" ብዬ አሰብኩ ብሎ ለታዳጊዎች መሰጠት ስላለበት ትኩረት አስተያየቱን አቅርቧል፡፡

በግል ደምሴ ሲዘግብ እጅግ ስሜታዊ ይሆንብኛል፡፡ አንዳንዴ የኳስ እንቅስቃሴ ካመጣው ውጤት እሱ የሚያጋባው ስሜት ይበልጣል፡፡ ብሔራዊ ቡድናችን ለ15ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ይመስለኛል ወደ ቶጎ ይጓዛል፡፡ በወቅቱ አብሮ የተጓዘው ደምሴ ነበር፡፡ የቶጎ ብሔራዊ ቡድን ተጫዋቾች ረዣዥሞች ነበሩ፡፡ የሜዳው ድባብ ደግሞ በጣም የሚያስጨንቅ ነበር፡፡ በፒካፕ መኪና ተጭነው የሚጨፍሩ ሰዎች ጨዋታው ከመጠናቀቁ በፊት ሜዳውን ይዞሩ ነበር፡፡ ጨዋታው ተጀመረ፡፡ የኛ

ቡድን ረዣዥም ኳሶችን በሰማይ መጫወት ጀመሩ፡፡ "ኧረ በመሬት ተጫወቱ፤ ማን ይንገራቸው እኔ እንደሆነ እዚህ ሣጥን ውስጥ ነው ያለሁት" በማለት ነበር ምንም ማድረግ እንደማችል የገለፀው፡፡ በወቅቱ ቶጎ አሸንፋ ለተከታዩ ዙር አልፋለች፡፡

ጅማ ከተማ በጭለማ ከተዋጠች አንድ ሣምንት አለፈ፡፡ 1982 መስከረም(?) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ለአፍሪካ ዋንጫ ጨዋታ የማጣሪያ ግጥሚያውን ከግብጽ ብሔራዊ ቡድን ጋር ለማድረግ ወደ ካይሮ ተጉዟል፡፡ ቡድኑ በሀገር ቤት ከመነሣቱ በፊት በሰጠው መግለጫ ውጤቱን አጥብቦ ለመምጣት ጥረት እንደሚያደርግ ገልጿል፡፡

ጅማ ከጨዋታው ቀድሞ መብራት ይመጣ ዘንድ ያደረገችው ፀሎት አለሰመረም፡፡ እሁድ ቀን የባትሪ ድንጋይ ዋጋ ጣሪያ ነካ፡፡ ጀነሬተር ያላቸው መስሪያ ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ አንዳንድ አርበኛ ሠራተኞች ባደረጉት ጉትጎታ ሥራ አስኪያጅ ቢሮ የተቀመጡ ቴሌቭዥኖች ወጥተው "ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ" ዓይነት ሆኑ፡፡ ጨዋታው በኢትዮጵያ ሠዓት አቆጣጠር ከምሽቱ 4:30 ጀምሮ በሬዲዮና በቴሌቭዥን በቀጥታ መተላለፍ ጀመረ፡፡

የዚያን ቀን የግብጾች ፍጥነት ተጫዋቾችን ብቻ ሣይሆን ደምሴንም ግራ ያጋባ ነበር፡፡ መናገር እስኪቸገር ድረስ በተደጋጋሚ የግብጽ ተጫዋቾችን ፍጥነት ያደንቅ ነበር፡፡ በተለይ ወንድማማቾቹ ሁለት ቁጥር የለበሰው የክንፍ ተጫዋችና 9 ቁጥር የለበሰው አጥቂ፡፡ የጨዋታው የመጀመሪያ ግማሽ ከማለቁ በፊት ይመስለኛል ሶስተኛው ጎል ገባ፡፡ ይህች ጎል ደምሴን በጣም ያስደመመች ነበረች፡፡ "ሰባት ቁጥር በክንፍ" እያለ ነበር ደምሴ "ይህ ሰባት ቁጥር በጣም ፈጣን ነው፡፡ ምን እሱ ብቻ ሁሉም በጣም ይፈጥናሉ . . . ሰባት ቁጥሩ ሰባት ቁጥሩ እያታለለ ነው፣ እያታለለ ነው፣ . . . አሻማ ግሩም ግብ፡፡ በጣም ግሩም ግብ፡፡ ግብ ጠባቂያችን ምንም ማድረግ አይችልም፡፡ ሰባት ቁጥሩ ከክንፍ ያሻማትን ኳስ ዘጠኝ ቁጥር እንደመጣች በቀጥታ ወደ ግብ በዓየር ላይ ነው የመታት ድንቅ ግብ የሚገርም ግብ ነው. . . . ብሔራዊ ቡድናችን በዓየሩም በምግቡም በምኑም ማሣበብ አይችልም ሙሉ ለሙሉ ተበልጧል፡፡ ይገርማል"

ጋቦሮኒ ላይ በተደረገው የአፍሪካ ታዳጊዎች ዋንጫ ጥሩ ተፎካካሪ የነበረው የነ ስንታየሁ ቆጬ ብሔራዊ ቡድን የመጀመሪያ ጨዋታውን ያደረገው ከጋና አቻው ጋር ነበር፡፡ ጨዋታን የሚጀምረው የጋና ብሔራዊ ቡድን ነበር፡፡ የጋና ሁለት ተጨዋቾች ጨዋታውን ለመጀመር መሐል ሜዳ መቆማቸውን ገልጾ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አሰላለፍን እያስተዋወቀ ነበር፡፡ ማስተዋወቁን አቋረጠና "የመሐል ዳኛው ጨዋታውን ለማስጀመር ፊሽካ ነፉ የጋና ዘጠኝ ቁጥር ለ አስር አሥር ቁጥሩ ፤ እንዴ . . . እህ ምን እያደገ ነው፤ ኧረ በጣም ይገርማል፡፡ አዎ ጨዋታው በተጀመረ በ. . . ሰከንድ ከመሐል ሜዳ የተጀመረውን ኳስ አስር ቁጥሩ በረዥሙ ለ. . . አቀብሎ የጋና ብሔራዊ ቡድን የመጀመሪያውን ግብ አስቆጥሯል፡፡ የኛ ተጫዋቾች ቦታ ቦታቸውን እንኳን አልያዙም . . . ." በዚህ ጨዋታ 4 ለ 1 የተሸነፈው ታዳጊው ብሔራዊ ቡድን ቀጣይ ጨዋታውን ያደረገው ከማሊ ጋር ነበር፡፡ በዚህ ጨዋታ ቡድናችን 4 ጎል አግብቶ አሸንፎ ነበር፡፡ ታዲያ አራተኛው ጎል ሲገባ ደምሴ ምን አለ "ብድሩን የማይመልስ ወንድ አይወለድ"

## ደምሴና የዓለም ዋንጫ

በ1982 የስፔን የዓለም ዋንጫ ከፍተኛ ክስተት ይሆናል ተብሎ በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው የያኔው የ18 ዓመት ጎረምሣ ዲያጎ አርማንዶ ማራዶና ጓደኛው ላይ የተሰራን ጥፋት መታገስ አቅቶት በመራገጡ በቢጫ በቀይ ካርድ ተሠናበተ፡፡ በተሰለፈባቸው የማጣሪያ ጨዋታዎች ባሣየው የአብዶ ጥበብ የሰዉን ስሜት ቀስቅሶ የነበረው ማራዶና የተጠበቀውን ያህል ክስተት ሣይሆን ቀረ፡፡ ይሁን እንጂ በእድሜና በጨዋታ በስሎ ከ4 ዓመታት በኋላ በሚክሲኮ የዓለም ዋንጫ ላይ ተመልሶ መጣ፡፡ በዚህ የዓለም ዋንጫ ወቅት ማራዶና ሙሉውን የውድድር ጊዜ ኮከብ ሆኖ ነበር የጨረሰው፡፡

በዚህ ውድድር ወቅት የተከሰተ ሌላም አሣዛኝ ክስተት ነበር፡፡ አፍሪካን በዓለም ዋንጫ ከወከሉት ቡድኖች አንዱ የአልጀሪያ ብሔራዊ ቡድን ነበር፡፡ የአልጀሪያ ብሔራዊ ቡድን በወደሚቀጥለው ዙር ለማለፍ የጀርመንና የኦስትሪያን ጨዋታ ውጤት ይቀብቃል፡፡ ሁለቱ ቡድኖች ግን ከአቅም በታች በመጫወት የዓለም ኳስ አፍቃሪን ያሣዘነ ደባ ፈፀሙ፡፡ አልጀሪያ ወደቀች፡፡ ሰለዚህ አሣፋሪ ድርጊት ደምሴ በሚገርም የአነባባብ ስልት እና የማጀቢያ ሙዚቃ ዘገባ አቅርቧል፡፡

ማራዶናን አስመልክቶ ደምሴ በወቅቱ ተወዳጅ ለነበረው የቅዳሜ መዝናኛ አንድ ፕሮግራም ሰርቶ ነበር፡፡ ይህ ዘገባ አጠቃላይ የሜክሲኮ የዓለም ዋንጫ ላይ ያተኩር እንጂ ርዕስ ጉዳዩ አድርጎት የነበረው የወቅቱን ፈርጥ ተጫዋች ዲያጎ አርማንዶ ማራዶናን ነበር፡፡ ታዲያ ደምሴ የማራዶና አድናቆት ቢበዛበት ሀገራዊውን ዘፈን ከልሶ (Re-Mix) ከስቱዲዮ ታዳሚዎች ጋር አዚሞለታል፤

በሸዋ ላይ ደሴ ታቹን በአርጀንቲና
ናና ማራዶና፡፡

## ደምሴና የአፍሪካ ክለቦች ሻምፒዮና ተሣትፏችን

የአፍሪካ ክለቦች ሻምፒዮና ሲነሣ የክለቦቻችን ተሣትፎ ብዙም የሚያኮራ አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ቡድን በአንድ ወቅት እስከ ሩብ ፍፃሜ ደርሶ ነበር መሰለኝ፡፡ አንዳንዴ ኳሱ ቀርቶ በስታዲየም ተመልካች የተረብ ውድድር ብንሣተፍ ይሻለን ይሆን የሚል ሐሣብ መታ ያደርገኛል፡፡ በአንድ ወቅት የኛው ቅዱስ ጊዮርጊስ ከቱኒዚያው ኤስፔራንስ ጋር ለማጣሪያ ተደለደለ፡፡ የቱኒዚያው ቡድን አዲስ አበባ ላይ ባደረገው የመጀመሪያ ጨዋታ 3 ለ 2 ተሸነፈ፡፡ የእንግዳው ቡድን አሰልጣኝ በውጤቱ አልተከፉም፡፡ ጥሩ ውጤት ነው ያገኘነው፡፡ አገራችን ላይ 3 ለ 0 በማሸነፈ ወደ ሚቀጥለው ዙር እናልፋለን ብለው ለአገራችን የቴሌቭዥንና የሬዲዮ ጋዜጠኞች ይናገራሉ፡፡ እንዳሉትም ሆነ፡፡ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ጋር ወደ ቱኒዚያ ተጉዞ የነበረው ደምሴ ሲመለስ ሰፋ ያለ ዘገባ አቀረበ፡፡ “. . .  የኤስፔራንስ አሠልጣኝ አዲስ አበባ ላይ በተደረገው ግጥሚያ ቡድናቸው ስላገኘው ውጤት ስንጠይቃቸው በመልሱ ጨዋታ 3 ለ 0 እንደሚያሸንፉ ተናገረው ነበር፡፡ ቱኒዚያ ላይ በነበረው ጨዋታ ሶስተኛው ጎል ቅዱስ ጊዮርጊስ ላይ የተቆጠረው 65ኛው ደቂቃ ላይ ነበር፡፡ የሚገርመው ቀሪዎቹን 25 ደቂቃዎች የቱኒዚያው ቡድን ተደጋጋሚ የማግባት እድል ቢያገኝም ግብ የማስቆጠር ፍላጎት የነበረው አይመስልም፡፡ እንደተናገርነው ሶስት ጎል አስቆጥረናል ከዚህ በላይ ምን ያደርግልናል የሚሉ ይመስል ነበር፡፡ ኧረ ጎበዝ የትንቢት ድቤያቸውን ደለቁብን እኮ”

## ደምሴና የአዲስ አበባ ከፍተኛ ዲቪዚዮን

የአዲስ አበባ ክለቦች ሻምፒዮን፣ አዲስ አበባ አንደኛ ዲቪዚዮን፣ ከፍተኛ ዲቪዚዮን፣ ሱፐር ሊግ፣ ፕሪሚየር ሊግ፣ አሁን ደግሞ መለስ ዋንጫ፡፡ የክለቦች የእግር ኳስ ውድድር ስያሜ ያለፈባቸው ስሞች ናቸው፡፡ በ1970ዎቹ መጨረሻ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ዲቪዚዮን የጦዘበት ወቅት ነበር፡፡ በዚያን ዘመን ከነበሩት ክለቦች መካከል ኪራይ ቤቶች አስተዳደርና እርሻ ሰብል አንድ ወቅት ላይ በጣም ገንነው ነበር፡፡ በአንድ ዓመት መርሐግብር የመጀመሪያው ዙር ላይ በጫወታ ማማር፣ በቅንጅት፣ ኪራይ ቤቶች የተዋጣለት ቡድን ቀርቧል፡፡ ታዲያ በተደጋጋሚ ስለዚህ ቡድን ጥሩ ጥሩ ዘገባ ሲሰራ ቆየና አንደኛው ፕሮግራም ላይ የክለቡን ስም በተደጋጋሚ ማንሣቱ ተሰማው መሠል “ደምሴ ምን ነካው ቤት ፈልጎ ነው ወይ አስሬ ኪራይ ቤቶች የሚለው እንዳልባል” በተመሣሣይ ዓመት ሁለተኛ ዙር ጨዋታ ላይ እነ ኃይላትን፣ መንግስቱ ሁሴንን፣ ዓለም፣ ፀጋዬ፣ እና ሌሎችም ጠንካራ ወጣቶች የተዋቀረው እርሻ ሰብል ብርቱ ተፎካካሪ ሆነ፡፡ በተመሣሣይ መልኩ ጥሩ ዘገባዎችን ስለ እርሻ ሰብል የሰራው ደምሴ የመጀመሪያውን ዙር የኪራይ ቤቶች ዘገባ ስጋት በማስታወስ “አሁን ደግሞ በእህል መጣ እንዳልባል” ሲል ፈገግ አሰኝቶናል፡፡

በየሣምንቱ ሰኞ ማታ ቅዳሜ እና እሁድ የተካሔዱ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ዲቪዚዮን ጨዋታዎችን ዘገባ ሲያቀርብ የቋንቋ አጠቃቀሙ፣ የሁኔታዎች አገላለፁ እጅግ መሣጭ ነበር፡፡ በኳስ እንቅስቃሴ ወቅት በቶሎ ወደ ቀኝ ወይንም ወደ ግራ መዞር የማይችልን አንድ ተጫዋች “ቆዳ እንደጫነ መኪና ለመዞር ሰፊ ቦታ ይፈልጋል” በሚል ገልፆት እንደነበር ትዝ ይለኛል፡፡ አንድ ወቅት ላይ ተጫዋቾች ሁሉ ኳስ ወደ ሔደችበት አቅጣጫ እየተሣቡ ቦታቸውን መልቀቃቸውንና የጨዋታውን ቅንብር ማጥፋቱ ቢያሣስበው “አንዳንዴ ግብ ጠባቂ የለጋትን ኳስ አባራችሁ ያዙ የተባለ ይመስል . . .” ብሎ ነበር፡፡

የሁሌው እንግዳ ሞት ዛሬ ደግሞ ደምሴ ዳምጤን አሣጣን፡፡ ሴ ላ ቪ እንዲሉ ፈረንሣዮች፤ ሕይወት እንዲህ ናት፡፡ ለወዳጅ ዘመዶቹ መጽናናትን እመኛለሁ፡፡ የሐዘናችሁ ተካፋይ ነኝ፡፡

አያልቅበት አደም
ጥቅምት 27 ቀን 2005 ዓ.ም.